# ለወገን ሁሉ ማሳሰቢያ/ማስጠንቀቂያ

## በሀገር ወዳድነት ሽፋን የወያኔ ሴራ

የሀገራችንን መሬት ለሱዳን የሰጠው ከሀዲ የወያኔ ቡድን ይህን ወንጀሉን ሊያጋል ጡና ሊቋቋሙ የተነሱትን ሀገር ወዳዶች ለማጥቃት ሰርጎ ገቦቹን በኮሚቴ ደረጃ አ ደራጅቶ በየፊናው ማሰማራቱተደጋግሞ ተገልጧል። የድንበር ኮሚቴ በሚለው ው ስጥ የአዜብ ጎላ ጉዳይ አስፈፃሚ ግለሰብ፤ የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ዘመናይ ወያኔ፤ ለመለስ ዘናዊ ያደሩ ሆዳሞች ሁሉ ተደባልቀው መገኘታቸውን ደግመን ደጋግመን አጋልጠናል።

በአሁኑ ጊዜ በተለይ ሀገር ወዳዱን ዜጋ ከገንዘቡ ለመለየትና ዓይን ያወጣ ዝርፊያ ለ ማካሄድ ትላንት መሬት አልተሰጠም መረጃ አምጡ፤ የወያኔና የሱዳን ስምምነት የ ተባለው የፈጠራ ወሬ ነው ወዘተ ሲሉ የነበሩት መሰሪዎች ከመ ቅፅበት ተቆርቋሪ መስለው ኮሚቴ እየመሰረቱ ገንዘብ አምጡን ተያይዘውታል። ይህን ሀገርን የመጠበ ቅ ታላቅ ግዳጅ ለርካሽ ፖለቲካ ግባቸው ለማዋልም ድርጅቶችን በመከፋፈል የተሰ ማሩ ጥቂቶችም ሰልፍ ጠሪና አሰባባሰቢ መስለው ለመሰየም ሲሯሯጡ ይታያሉ። የሻዕቢያውን ርካሽ ቅጥረኛ ኤልያስ ክፍሌን ይጠቅሷል።ይህ ሁሉ በቸልታ ሊታለፍ የሚገባው ጉዳይ አይደለም። ከዚህ በፊት በልዩ ልዩ አስመሳይ ታጋዮች ገንዘቡን፣ ጊዜውንና ጉልበቱን ሲዘረፍ የቆየው በውጭ ሀገር ነዋሪ ዜጋ፥ እነዚህን የወያኔ መሳሪያዎችና ተራ ዘራፊዎች ወይም ርካሽ ፖለቲካን አራማጆች ማንነታቸውን አውቆ በማጋለጥ ሊያሳፍሯቸው ይገባል። ሀቀኛ ሀገር ወዳዶች፥የሀገራቸውን ግዛት ና ድንበር ከዜጎች ጋር ሆነው ለማስከበር በአስቸኳይ ሊደራጁም ይገባቸዋል። ግርግር ለወያኔ ያመቻልና ሁላችንም ዘብ እንቁም።

ጎራችን ከወያኔ ቅጥረኞችና ርካሽ ፖለቲካ አራማጆች ይፅዳ!!
የሀገርን ድንበር ለማስከበር ሀቀኛ የኢትዮጵያ ልጆች እንተባበር!!